# ጽንፈኞቹ ቢጫውን ካርድ ያሳዩት ለማን ነው?

**ዮናስ** 10/15/12

ምንም እንኳ በአደረጃጀት፣ በአወቃቀርና በመዋቅር ስፋት ይለያዩ ይሆን እንጂ በኢትዮጵያ የኃይማኖት እኩልነት፣ የእምነት ነፃነት ከተረጋገጠና ህገ መንግሥታዊ ዋስትና ካገኘ በኋላ ሁሉም ኃይማኖቶች ማለት ይቻላል ኃይማኖታቸውን የሚያፀኑበትና የሚጠብቁበት፣ እምነታቸውንም በነፃነት የሚከውኑበት እና አስተዳደራዊ ሥራዎችን የሚፈፅሙበት ተቋማት ገንብተዋል፣ የአሠራር ሥርዓትም እንደየእምነታቸው ፍልስፍና ዘርግተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የእምነቱ ተከታዮች ከሚያመልኩባቸው አብያተ ክርስቲያናት ባሻገር በርካታ ኃይማኖታዊ ትምህርቶች የሚሰጡባቸው ተቋማትና አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚከወኑበት መዋቅሮች አሉ፡፡ በኃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሣኔ አሳላፊ ከሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ ጀምሮ አስተዳደራዊ ሥራዎች በሚከናወኑበት የጠቅላይ ቤተክህነት፣ የየሀገረ ስብከት እና የየአብያተ ክርስቲያናት ጽህፈት ቤቶች የተደራጀች ናት፡፡ በእነዚህ ተቋማትም ሰፊ የሆነ የሰው ኃይልና ኃይማኖታዊ መመሪያዎችና ደንቦችን ፈጻሚ ሠራተኞች አሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከመዋቅሩ ውጪ ሌላ ጠምዛዥና አዛዥ የሆነ ማንኛውም አካል ጣልቃ ሊገባ እንደማይችል ህገ መንግሥቱ ላይ ከመደንገጉም በላይ ኃይማኖቱም በመንግሥት ጉዳይ ላይ እጁን የማስገባት መብት የለውም፡፡

በነገራችን ላይ ለማሣያ ያህል አነሳሁት እንጂ መዋቅሩ፣ አደረጃጀቱና የአፈጻጸም ሥርዓቱ /ቢሮክራሲው/ ሰፊና ጥልቅ ነው፡፡ አጠቃላይ ግቡ ግን ኃይማኖቱን መጠበቅ፣ የእምነቱ ተከታዮች መንፈሣዊ አገልግሎት በአግባቡ እንዲያገኙ ማድረግና በእግረ መንገድም ልማታዊ ሥራዎችን በማከናወን ሀገሪቱን ከድህነት በማላቀቅ ሂደት ላይ ተሣትፎ ማድረግ ናቸው፡፡ ለኦርቶዶክስ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ኃይማኖቶች ፍልስፍና ሀገር ከሁሉም በላይ ቀዳሚ ነው፡፡ ሀገር ከሌለ፣ ድህነት ሥር ከሰደደና ልማት ካልተረጋገጠ የኃይማኖቶቹም ህልውና አደጋ ላይ የሚወድቅ ከመሆኑ ባሻገር የሀገር ጉዳይ መንፈሣዊ ተልዕኮም ጭምር በመሆኑ ነው።

ልክ እንደዚሁ ሁሉ በእሥልምና ኃይማኖትም ሰፊና ጥልቅ የሆነ ኃይማኖታዊ አደረጃጀትና መዋቅራዊ ተቋማት አሉ፡፡ ኃይማኖቱ የሚፀናበትና አማኒያን የሚመሩበትም መንፈሣዊ መመሪያና ደንቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ የእምነቱ ተከታይ መሆንን የሚጠይቅ አይመስለኝም፡፡ ምንም እንኳን ስለ እሥልምና እምነትና ኃይማኖት (ተከታይ ባለመሆኔ) ጥልቅ የሆኑ መንፈሣዊ ጉዳዮችን ማወቅ ቢሳነኝም ያነሳሁትን ርዕሰ ጉዳይ ለማብራራት ግን ህገ መንግሥታዊ ግንዛቤ መያዝና ታሪካዊ እውቀት በቂ ስለሚሆን ላለፉት ስምንት ወራት ከእሥልምና እምነት፣ ፍልስፍናውና ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች ጋር ተያይዞ በእምነቱ ተከታዮች ነገር ግን ጥቂት በሆኑና ራሳቸውን የአወሊያው ኮሚቴ በሚል በሰየሙ አካላት ሲነሱ የነበሩ መነባነቦችንና የመጅሊሱን ምርጫ እቃኛለሁ፡፡

ቀደም ብዬ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ በኩል ያነሳሁት አደረጃጀት በእሥልምና እምነት ውስጥም ሊኖር እንደሚችል አልጠራጠርም፡፡ ለአብነት እና የእምነቱ ተከታዮች ያልሆኑቱ ሁሉ የሚያውቁትን ብናነሳ እንኳ የእሥልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የሚባለው ተቋምና አመራሩ የኃይማኖቱ የመጨረሻ ውሣኔ ሰጪ አካልና አስተዳደራዊ ሥራዎችን በበላይነት የሚመሩ ናቸው፡፡ ይህን እንደ ቅዱስ ሲኖዶሱ ጽህፈት ልንወስደው እንችላለን፡፡ በተመሣሣይም  እንደ ሀገረ ስብከቱ ጽህፈት ቤቶች ዓይነት  በየክልሉም ጠቅላይ ምክር ቤቶች ሲኖሩ እንደ አብያተ ክርስቲያናቱ ጽህፈት ቤቶችም በተመሣሣይ የመስጂዶች አስተዳደር ጽህፈት ቤቶች አሉ፡፡ እንደ ኦርቶዶክሱ ሊቃውንተ ጉባዔም የዑለማዎች ምክር ቤትን በእሥልምናውም በተመሣሣይ እናገኛለን፡፡

በአጠቃላይ ልክ እንደ ኦርቶዶክሱ ሁሉ እነዚሁም መዋቅሮች እና ተቋማት ኃይማኖታዊ ተልዕኮዎችን የሚወጡ ለአማንያኑ መንፈሣዊ አገልግሎት የሚሰጡ ስለሀገር፣ ሠላምና ልማት የሚፀልዩና ንቁ ተሣትፎ የሚያደርጉ፤ አማንያን በነፃነት ፈቅደውና አምነው ያለማንም አዛዥና ናዛዥ አላህን ማመስገን የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ሥራቸውና ተግባራቸው ነው፡፡ አወሊያ የተባለው ተቋም ደግሞ መንፈሣዊ ወስጋዊ ትምህርት የሚሰጥበትና የእምነቱ ተከታዮች በዓለማዊ እውቀት በልፅገውና ደርጅተው፣ ሥነ ምግባር ያላቸው፡ ቀና እና ሠላማዊ ዜጋ ሆነው እንዲወጡ የሚሰራ ታሪካዊ፤ ለኢትዮጵያም ሆነ ለእሥልምና እምነት ታላላቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ልሂቃኖችን ያፈራ ትምህርት ቤት ነው፡፡

የዛሬ ስምንት ወር ገደማ ግን ከአወሊያው ትምህርት ቤት አካባቢ የተሰማውና የተከናወነው ተግባር በእርግጥም አወሊያን ለሚያውቁት መላ ኢትዮጵያውያን አስደንጋጭና ግር  የሚያሰኝ ነበር፡፡

የአወሊያው ኮሚቴ ነኝ የሚል ቡድን የእምነቱን አራማጆች ከሁለት ከፍሎ ከፈረጀ በኋላ ኃላፊነቱ ጠቅላይ ምክር ቤቱን የሚመሩ አባቶችን በማውረድ በምትኩ እኛን ይወክላሉ ያልናቸውን አመራሮች ማስቀመጥ ነው አለ፡፡

መነሻ ምክንያቱ ሲል ሲያነሣ የነበረው ደግሞ መጅሊሱ የሥልጣን ዘመኑ ተጠናቋል የሚልና ከመንግሥት ጋር ይሞዳሞዳል  የሚል ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ  ለተጠቀሰው ምክንያት በማሳያነት ያቀረበው ደግሞ መጅሊሱ ከመንግሥት ጋር ተመሳጥሮ አህበሽ የተባለ አስተምሮ በኢትየጵያ እያስፋፋ ነው የሚል ነው፡፡

ዳሩ ግን  መንግሥትም ሆነ መጅሊሡ ይህ የአወልያው ጥያቄ ትክክልም ሆነ አልሆነ መቅረብ የሚችለው በሕጋዊ እና በሠላማዊ መንገድ እንጂ የወልያው ኮሚቴ በጀመረው የአመጽ መንገድ እንዳልሆነ ቢያስገነዝብም ኮሚቴው የመረጠው ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ ማለት ነው፡፡

በዚህ መሠረት ለዚሁ ተግባር ሲል በተደራጀና ከውጭ ባሉ የጥንስሱ ባለቤቶች አማካይነት መንግሥት እሥልምናን እየደፈረ፣ ሕገ መንግሥቱን በመጣስ  እጁን እያስገባ የእምነቱን ተከታዮች ነፃነት የተገፋ በማስመስል በየጋዜጦቹ እና የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ /ቪ.ኦ.ኤ/ን በመሰሉ የራዲዮ ጣቢያዎች በኩል ወሬ በማራገብ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ያለመረጋጋትን ከመፍጠራቸውም በላይ መንግሥትን ሥራ ሲያስፈቱ ቆይተዋል፡፡

መንግሥት በበኩሉ የእሥልምና ብቻ ሣይሆን ማናቸውም የእምነት ተቋማት በአደረጃጀታቸው አማካይነት ኃይማኖታዊ ትምህርቶችን የመስጠት መብት ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ነገር ግን በሕግ ወሰን ውስጥ ሆኖ ፀጥታ የማስከበር፣ የአዳራሽ አገልግሎት መስጠትን የመሳሰሉቱ ኃላፊነቴና ግዴታዬ ነው ሲል በመጅሊሱ በኩል ተሰጠ የተባለውም ሥልጠና በዚህ መንገድ መታየትና መወሰድ እንዳለበት በተለያዩ የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎች በኩል ገለጸ፡፡

ሆኖም ግን አወልያው ቀድሞም ቢሆን ዓላማው ሌላና ከበስተጀርባውም ሌላ አካል አለ ሲል መንግሥት እንደተናገረው የቀረቡለትን ሕጋዊ አማራጮችና መግለጫዎች ሁሉ አልቀበልም ሲል የባሰ ደነፋ፡፡

በዚሁ ላይ በአቋራጭ ሥልጣን ለመያዝ የሚሹትን ኃይሎች ጨምሮ በአሸባሪነት የተፈረጁት ግንቦት 7 እና ስደተኛው የተባለው ሲኖዳስ ሳይቀር ሕገ መንግሥቱ ይከበርልን ሲሉ እንዳላንጐራጐሩ ሁሉ የአወልያው ጥያቄ ሕገ መንግሥታዊ በሆነ መልክ ሊመለስ ይገባል ሲሉ መንግሥትን ለማሳጣት ያደረጉት ጥረት ኮሚቴውን ይበልጥ የልብ ልብ ሰጠው፡፡

በመሆኑም ዓርብ በመጣ ቁጥር መንፈሣዊ የሆኑትን እና መንፈሣዊነታቸው በመንግሥት ተደፍሯል የሚሏቸው መስጂዶችን ማወክና ማሳወክ፤ አልተከተለንም አይመስለንም ያሉትን አሚኒ ሳይቀር ማገትና መደብደብ ጀመሩ።

እዚህ ጋር አንድ ሊታለፍ የማይገባውና ሊታሰብበት የሚገባ መሠረታዊ ነገር ያለ ይመስለኛል፡፡ የአወሊያው ኮሚቴ ነኝ በሚል የሚንቀሳቀሰው ቡድን መንግሥት ሕገ መንግሥቱን በመጣስ ጣልቃ ገብቷል፡፡ የእምነት ነፃነታችንን ተዳፍሯል /አላስከበረም/ ስለሆነም መንግሥት በአስቸኳይ እጁን ያንሣ የሚል ጥያቄና አቤቱታ ሲያቀርብ፤ በተመሣሣይ ግን ኮሚቴው የሚፈጽመው ተግባር ሁሉ ፀረ ሕገ መንግሥት መሆኑን ለመስማት አለመፈለጉ ነው፡፡ የኮሚቴው ጀርባ ሌላ ነው የሚባለውም ለዚሁ ነው፡፡ ማሣያ ማቅረብ ይቻላል፡፡

ለምሣሌ አንተ አህበሽ ነህ፤ ስለሆነም የእኛ አይደለህም ብሎ አንድን ሙሥሊም መደብደብ ቀርቶ የእኛ ካልሆንክ ብሎ መነዛነዝም የእምነት ነፃነትን መጋፋት መሆኑን ኮሚቴው ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ነገር ግን አንድ የእሥልምና እምነት ተከታይ የፈለገውን ዓይነት እምነት የመለወጥና እስካለማመን የሚደርስ ነፃነቱ በሕገ መንግሥቱ ተረጋግጦለት ሳለ እሥልምና ውስጥም ሆኖ አህበሽ ነህ በሚል በኮሚቴው በኩል ድብደባና ስድብ ቀለቡ እንዲሆን ይገደዳል፡፡ ሌላም አለ መጅሊሱ የሥልጣን ዘመኑ አልቋል፣ አዲስ ምርጫ ይከናወን፤ ሲል የሚጠይቀው የአወልያ ቡድን መልሶ መንግሥት መጅሊሱን እንዲያወርድለት ይጠይቃል፡፡ በመሠረቱ መንግሥት ምርጫው በተሣካ ሁኔታ ይከናወን ዘንድ የሎጀስቲክስ እና የፀጥታ ድጋፍ ከማድረግ የዘለለ ተግባር መፈፀም አይችልም። ከዚህ ውጪ መንቀሳቀስ የእምነት ነፃነትን አለማክበር እና መንግሥታዊ ኃይማኖት የለም የሚለውን

ሕገ መንግሥታዊ ቃል ማጠፍ ነው፡፡ ነገር ግን መንግሥትን ውጣልን የሚለው ኮሚቴ መልሶ ግባና መጅሊሱን አውርድልን ይላል። ይህ ደግሞ የቡድኑ ዓለማ ሌላና ኃይማኖታዊ ያልሆነ ድብቅ አጀንዳ ነው የሚለውን ለማመን ያስችለናል፡፡

የሆነው ሆነና መንግሥት ብዙኃኑ ሙሥሊም ካለመረዳትና ከጫና ለመላቀቅ ሲሉ የእነዚህ ሰዎች ሰለባ እንዳይሆኑና የኮሚቴው ተልዕኮም እሥልምና ሳይሆን ፖለቲካ መሆኑን ለሙስሊሙ ከማስተማር ጐን ለጐን የጁምአን የፀሎት ሥርዓት ጸጥታ የማስከበር ተግባር መከወን፣ ከአወሊያው ኮሚቴ የተነሳውንና ትክክል የሆነውን የምርጫ ጥያቄ ምላሽ ያገኝ ዘንድ ሥልጣኑ ካለው መጅሊስ ጋር መክሮ ምርጫው በቀነ ገደቡ ይከናወን ዘንድ ኃላፊነቱን ተወጥቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ምርጫው በዚህ ቀን ምዝገባ ተጀምሮ በዚህ ቀን ይከናወን የሚለው ቀን ሲቆረጥ የአወሊያው ጀርባ ሌላ ስለሆነ ሌላ ጥያቄ በማንሣት ውዝግቡንና ግርግሩን ለማስቀጠል ከቀድሞው ጊዜ ባስ ያለ የብጥብጥ ስትራቴጂና የኮሙኒኬሽን ሥልት በመንደፍ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡

እንደ ሀሳቡና ፍላጐቱም ለዚሁ ተልዕኮ ባሰማራቸው ሚዲያዎች በኩል በተቃዋሚውም የግል ፍላጐት መነሻነት በመታገዝ ግርግሩን አበረታ፡፡ በየመስጂዶቹ የሚከናወኑ የአምልኮ ሥርዓቶችንም በከፋ ደረጃ ማወኩን ተያያዘው፡፡
በዚህ ጊዜ ሠላም የማስከበርና ፀጥታ የማስጠበቅ ሥልጣን የተሰጠው መጅሊሱ ሳይሆን መንግሥት በመሆኑ አፍራሽ ተልዕኮ ተሰጥቷቸው ሲንቀሳቀሱ የነበሩትንና በርካታ ምክሮች ተሰጥቷቸው አልታረም ያሉ በጥባጮችን በቁጥጥር ሥር አውሎ በህጉ መሠረት ጉዳያቸው እንዲታይ አደረገ፡፡

የአወሊያው ቡድን ፀረ ህገ መንግሥታዊ መሆን የሚገለጽበት ሌላም ነገር ቀጥሎ አጋጠመ፡፡ አዋኪ የነበሩት ኃይሎች በህጉ መሠረት ጉዳያቸው በሚታይበትና ነፃ በሆነው ፍርድ ቤት ቅጽር ግቢ ቡድኑ በመገኘት ያልተፈቀዱና በህገ መንግሥቱ የተከለከሉ የአምልኮ ሥርዓት ከመፈፀማቸውም ባሻገር የፍርድ ሂደቱን በጩኸትና ግርግር ማስታጓጎላቸውን ተመለከትን፡፡

ያም ሆኖ ህጉ በማይፈቅደውና ሌሎችም በእነዚህ ኃይሎች ተዝቆ የማያልቅ ከውጭ በሚገባ ገንዘብ ተታለው ወደእነዚህ ፀረ - ህገ መንግሥት ወደሆኑ ኃይሎች እንዳይቀላቀሉ መንግሥት በብዙኃን መገናኛዎቹ በኩል እና በእምነቱ ልሂቃኖች በኩል ማስተማሩን እና እውነታውን በማሣየት የእነዚህን ኃይሎች ድብቅ አጀንዳ ማጋለጡን ተያያዘው፡፡

ቡድኑ ግን አክራሪና ወደ ሽብርተኝነት ጐራ እያመራ ያለ ነበርና በየመገናኛ ብዙኃኑ በመገኘት ለሕዝበ ሙስሊሙ ትክክለኛውን እና የእምነቱን ፍልስፍና የሚሰብኩ ልሂቃንን በማግሥቱ በመስጂዶች ግቢ መደብደብና ማገት ተጀመረ፡፡ እንዲህ ዓይነት ፀረ ህገ መንግሥት ተግባራትን በሚፈጽሙ ኃይሎች ላይ አሁንም መንግሥት የአብዛኛው ሰው መቀላቀል ወይ በመታለል ወይም

በግንዛቤ እጥረት ወይ ደግሞ ኃይማኖታዊ ተልዕኮ መስሎት ሊሆን እንደሚችል በመገመት የማስታመምና የማባባል ሥራውን ቀጠለበት፡፡

ሆኖም ግን በእነ ሠለፊያ ጋዜጣና በእነ ቪኦኤ ላይ የሚለቀቁቱ ዘመቻዎች በእርግጥም የአገሪቱን ዜጐች ሉዓላዊ ሥልጣን የሚጻፈርና ለሽብርተኝነት በር የሚከፍት ሆኖ በማግኘቱ ያሰመርኩትን ቀይ መስመር አልፋችኋልና ቀይ ካርዱን እንኩ በሚል ወደ ትክክለኛ እርምጃና ውሣኔ አመራ፡፡ በነገራችን ላይ አንድ ነገር ይገርመኛል፡፡ በሽብርተኝነት ዜጐቻቸው ከተጐዱባቸው፣ በርካታ ተቋማት ከተናዱባቸው እና አሁንም ሥጋቱ ካልተላቀቃቸው እና ሽብርተኞች ካነጣጠሩባቸው አገራት ሁሉ አሜሪካንን የሚያህል የለም፡፡ ስለሆነም አሜሪካ ሽብርተኝነትን ለማስወገድና ለማድቀቅ ከሌሎች ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ሥራዎቿ ሁሉ አልቃ በመሥራት ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህም ለሽብርተኝነት እና ለሽብርተኞች ትዕግሥትና ርህራሄም እንደሌላት እየተመለከትን ነው፡፡ ሆኖም በሀገረ አሜሪካ የሚገኘውና በአሜሪካ መንግሥት ሙሉ ድጋፍ የሚሰራው ቪኦኤ ለሽብርተኝነት መመንጠር ሳይሆን መጠናከር እየሰራና በአፍሪካና በተለይም ለአሜሪካ የፀረ - ሽብር ዘመቻ የላቀ አጋርነት ባላት ኢትዮጵያ የሚታዩ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴዎችን እየደገፈና እያበረታታ፣ ለመጐልበታቸው ሽፋን እየሆነ አሜሪካ ሠምታ እንዳልሰማችና አይታ እንዳላየ መሆኗ በእርግጥም የሚገርመኝ ጉዳይ ነው፡፡

የሆነው ሆኖ መጅሊሡ የሥልጣን ዘመኑ እንዳበቃ በመገንዘብ እና በማመን ኃይማኖታዊ ትዕዛዛቱ እና የምክር ቤቱን ህግጋት መሠረት በማድረግ መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም ምርጫው ይከናወን ዘንድ ቀን ሲቆርጥ ኮሚቴው አሁንም ወደማያልቀው የተለየ ጥያቄ አመራ፡፡ "ምርጫው መከናወን ያለበት በመስጂድ ነው" የሚል ጥያቄ አይሉት ውሣኔ አሳለፈ፡፡

በዚህ ምርጫው በመስጂዶች ይሁን? ወይስ በቀበሌ እና በወረዳ መዋቅሮች? በሚለው ሙግት ላይ ምርጫውን የማስተባበር ኃላፊነት የተሰጠው የኡለማዎች ምክር ቤት በቂና አሳማኝ የሆኑ ዝርዝር ማብራሪያዎች ቢሰጥም ኃይማኖታዊው እውቀት የሌለንም እንኳን ብንሆን በተለይም የማያልቀውን የአወልያ ኮሚቴ ጥያቄ አንድ በአንድ የተከታተልን ሰዎች ምርጫው በመስጂዶች መከናወን እንደማይኖርበት ማረጋገጥና ምክንያታዊ ምስክርነት መስጠት ይቻለናል፡፡

ለምሣሌ የማዕከላዊ እስታትስቲክስ ባለሥልጣን በሰጠው መረጃ መሠረት ከሙስሊሙ ቁጥር ጋር የተመጣጠኑ መስጂዶችና የሥርጭታቸውም አማካይ ቦታ ላይ የመገኘትን ጥያቄ ማንሣት አንዱና የምርጫውን በመስጂዶች ይካሄድ የማለውን ጥያቄ ውድቅ ያደርግልናል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት መስጂዶች ማምለኪያና መንፈሣዊ ቦታዎች ወይስ የምርጫ ቦታዎች? ብለን መጠየቅም ሌላው የኮሚቴውን የማወዛገቢያ ጥያቄ ውድቅ የሚያደርግ ነው፡፡ እዚህ ጋር ግን እሥልምና እንዲህ የሰፋ መዋቅር እና የተጠናከረ አደረጃጀት ባልነበረበት ጊዜ የአማንያኑም ቁጥር

እንዲህ የበዛና አሰፋፈሩም እንዲህ ባልተንቦረቀቀ ጊዜ ድጋፍ ሰጪ መንግሥት ባልነበረ ጊዜ ከዚህ በፊት ምክር ቤቱ ምርጫ በመስጂዶች አከናውኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ነገር ግን አማንያኑ በኃይማኖታዊ እውቀት ደርጅተው ተቋማዊ መዋቅራቸውም በተጠናከረ ቁጥር እምነቱን ከሚያራክሱ አሠራሮች መውጣትና ኃይማኖታዊ ግዴታዎችን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ስለሆነም እሥልምና በደንቡ እና መመሪያው መሠረት መምረጥ ለሚችሉ አማንያን ሁሉ የመምረጥ መብታቸውን መስጠት ያለበት በመሆኑ አወልያው የሴቶችን ተፈጥሮዓዊ ጉዳይ እንደምን ዘንግቶት ነው በመስጂዶች ካልተከናወነ ብሎ እምቧ ከረዩ የሚለው ካልን አጀንዳው ድብቅ መሆኑ ላይ እንደርስበታለን፡፡

ሌላው ደግሞ በዚያኑ ሰሞን እንዳየነው ከእኛ አይደላችሁም፤ በሚዲያ ተናግራችኋል የተባሉ ግለሰቦች በየመስጂዶቹ ግቢ ሲደበደቡና ሲታገቱ ቅጽር ግቢዎቹ ለፀጥታ ኃይላት የተከለከሉና የማይፈቀዱ በመሆናቸው የዜጎች ደህንነት አደጋ ላይ ወድቆ እንደነበር አንዘነጋም፡፡

ምርጫ ደግሞ ዓለማዊ ጉኑ የሚያደላና የፀጥታና ደህንነት ጉዳይን ከምንም ነገር በላይ የሚሻ ክንውን መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ምርጫው በመስጂዶች ቢከናወንና የማጭበርበር ሙከራዎች ቢደረጉ ሊነሳ የሚችለውን ትርምስና ፀብ ማን ሊያስብከብር ነው? ብለንም በመጠየቅ የአወልያው ጥያቄዎች ሁሉ አይረቤና ጀርባቸው ሌላ እንደሆነ መረዳት ያስችለናል፡፡ ስለሆነም በምርጫ አስተባባሪዎች ምክር ቤትና በመላው ሙሥሊም ዘንድ ምርጫው በቀበሌና ወረዳዎች እንዲከናወን ከመግባባት ላይ ሲደረስ አወልያውና እነ ቪኦኤ ዳግም ወደ ሌላ ቅስቀሳ አመሩ ። "ምርጫው ሙሥሊሙን የማይወክልና የመንግሥት እጅ ያለበት ነው" ሲሉ ሕዝበ ሙሥሊሙ ለምርጫ እንዳይወጣ ከመቀስቀስ ጀምሮ የምርጫው ዋዜማ በሆነው የጁምአ ፀሎት ላይ የቢጫ ማስጠንቀቂያ ከርድ ለመንግሥት አሳዩ፡፡

ሆኖም ይህ አፍራሽና የኃይማኖትን ለምድ የለበሰ ኮሚቴ ቀድሞ በመንግሥት ቀይ ካርድ የተሰጠው መሆኑን ቢገነዘብ ኖሮ ማስጠንቀቂያ ቢጫ ከርዱን በራሱ ላይ የመዘዘው እንደሆነ ባልጠፋው በነበር፡፡

ለማናቸውም የመጀሊሱ ምርጫና የምርጫ ሥርዓት ጥቆማ ከመስጠትና ከመምረጥ ጀምሮ እዚያው ተጀምሮ እዚያው የሚያልቅ በመሆኑ ለማጭበርበር ካለመመቸቱም በላይ ለፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አብነት መሆን የሚችል የአሠራር ሥርዓት ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ከበርካታ መገናኛ ብዙኃን እንደተመለከትነውና እንደሰማነው አብዛኞቹ ተመራጮች ሊመርጡ የሄዱና ሳያስቡት ተጠቁመው የተመረጡ፤ አንዳንዶቹም ኃላፊነቱን መሸከም በተለያየ

ምክንያት ይከብደናል ሲሉ ከእጩነት ራሳቸውን ያገለሉ ናቸው፡፡ አወልያው ተማትሮ ቢሆን ሊመረጥ እንደሚችልና እድሉን "ሚስ" እንዳደረገ ቢነገርም በእኔ በኩል ግን የአወልያው ጥያቄና ፍላጐት ሌላ በመሆኑ አለመሣተፉን እድሉን "ሚስ" እንዳደረገ አልቆጥረውም። ይልቁንም በራሱ ላይ የመዘዘውን የቢጫ ካርድ መነሻ በማድረግ መላው የሙሥሊሙ ማኅበረሰብና አዲሱ መጅሊስ እንዲሁም መንግሥት ለዚህ ኮሚቴ በተግባር የሚገለጽ የቀይ ካርድ ሊያሳዩት እንደሚገባ እመክራለሁ።